# የኢትዮጵያ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ህብረት (ኢተፖድህ)
## መግለጫ

## ሁለት ወገኖች ከማይሞግቱበት ኮሚሽን የኢትዮጵያ ህዝብ ምንም አይጠብቅም!

January 29, 2002

ለኢትዮጵያና ኤርትራ የድንበር ውዝግብ መፍትሄ ለመሻትና ይግባኝ የሌለው የመጨረሻ ውሳኔ ለመስጠት በሄግ ከተማ የተቀመጠው አለም አቀፍ የሽምግልና ኮሚሽን «ሁለቱም ወገኖች» አቀረቧቸው የተባሉትን የመከራከሪያ ነጥቦች ሰምቶ ከጨረሰ በኋላ ባሁኑወቅት እነዚህን ክርክሮችና መረጃዎች በመመርመር ላይ መሆኑንና የመጨረሻ ውሳኔውን በፊታችን የካቲት አጋማሽ ላይ ለመስጠት እየመከረ መሆኑን ታውቋል።

ከሶስት አመታት በፊት የሻብያ አመራር መቸም ጊዜ ቢሆን ከኢትዮጵያ አስተዳደር ስር ወጥተው የማያውቁትን ግዛቶች በእብሪት ወርሮ ሲቆጣጠር ኢተፖድህም ሆነ ሌሎች የሃገራችን ዴሞክራቶችና የሰላም ሃይሎች በዚህ በማንኛውም መስፈርት የአለም አቀፍን ህግጋት ጥሶ በተፈጸመ የሃይል እርምጃ ሳቢያ ሊከሰት የሚችለውን ከባድ ውድመት ከወዲሁ በመመዘን ከህግም፣ ከሞራልም አንጻር ሊኖር የሚችለው አንድ መፍትሄ «የሰላሙን ቁልፍ የያዙት የሻብያ የጦር አበጋዞች» በሃይል ከያዙት ግዛት ጦራቸውን አውጥተው ጉዳዩ በወቅቱ የተለያዩ መንግስታትና አለም አቀፍ ተቋማት ባቀረቡት ሰላማዊ ድርድር ላይባተኮረ አለም አቀፍ የፍርድ ተቋም የሁለቱንም ወገኖች የይገባኛል መከራከሪያዎች አዳምጦው በሚያቀርበው የማስታረቂያ ሃሳብ መሰረት እንዲፈታ ተደጋጋሚ ጥሪ አስተላልፈዋል።

የሸአብያ መሪዎች እነዚህን ጥሪዎች ለሁለታ አመታት ያህል አሻፈረን ብለው በፈቃዳቸው ወደ ሰላማዊ ድርድር እን[illegible]ም በማለታቸው በደርዘን ሽ የሚቆጠሩ የኢትዮጵያና የኤርትራ ወጣቶች ህይወት በወደመባቸው ጦርነቶች በሃይል የያዟቸውን ግዛቶች ለቀው ወደ አልጅርሱ ድርድር እንዲመጡ ተገደዋል።

በጠረጼዛ ዙሪያ ድርድር ተደርጎ ይህ አውዳሚ ጦርነት ለጊዜውም ቢሆን መገታቱ ልጆቹን በገፍ በመገበር ላይ ለነበረው የኢትዮጵያም ሆነ የኤርትራ ህዝብ ትልቅ እፎይታን ያመጣ ሂደት መሆኑ አይካድም። ድርድር ሲባል ማንም ኢትዮጵያዊ የገባውም ሆነ የጠበቀው የሃገራችንን ታሪካዊ መብትና ጥቅም ህዝቦችዋም ለነዚህ መብቶችና ለሃገራቸው የከፈሉትን ከባድ መስዋእትነት ከሁሉም አንጻር መርምሮና አመዛዝኖ ፍትሃዊ ብያኔ የሚገኝበት ሂደት እንደነበረ ግልጽ ነው። አሁን የሚታየው ግን ከዚህ የህዝባችን ጉጉት ምንም ግንኙነት የሌለው አካሄድ ነው። በልጅርሱ ስምምነት መሰረት ከተቋቋው የሽምግልና ኮሚሽን ኢትዮጵያ ምንም በጎ ነገር መጠበቅ አትችልም። በግልጽ እየታየ እንደመጣው ከሆነ በመከሰት ላይ ያለው ሂደት በጦር ሜዳ በደርዘን ሽ የኢትዮጵያ ልጆች መስዋእትነት የተሸነፈውና በነአቶ መለስ ዜናዊ ትብብርና በአለም አቀፍ ወገናዊ ግፊት ጨርሶ ከመደቆስ ያመለጠው የሸአብያ አገዛዝ በጦር ሃይል ተዋግቶ፣ ካለም አቀፍ ህግጋትና ውሎች አሰራርና አስገዳጅነት አንጻር ተከራክሮ፣ ከህዝቦች መብትና፣ ከታሪክ ሃቆች እየተነሳ ተሟግቶ ለማግኘት የማይችለውን ድል የኢትዮጵያ ህዝብ በማያውቀውና ባልመከረበት ሁኔታ በምስጢር በተደረጉ ጸረ ኢትዮጵያ ስምምነቶች አማካኝነት ለማግኘትና ለነዚህ ስምምነቶች አለም አቀፋዊ ቡራኬ ለማጎናጸፍ የሚሞከርበት ሂደት ነው።

ማንኛውም የፍርድም ሆነ የሽምግልና ሂደት ተአማኒነትም ሆነ አስገዳጅነት ሊኖረው የሚችለው የሚዳኙም ሆኑ የሚሸመገሉ «ሁለት ወገኖች» ሲኖሩና የነዚህ ወገኖች መረጃዎችና መከራከሪያዎች በተሟላ መልክ ቀርበው መመርመራቸው ሲረጋገጥ ብቻ ነው። የዚህ የሽምግልና ኮሚሽን አሰራር በወያኔና ሸአብያ መሪዎች ጸረ ኢትዮጵያ ሴራ ሆን ተብሎ ከዚህ መሰረታዊ መርህ እንዲርቅ የተደረገ አሰራር ነው።

የኢህአዴግም ሆነ የሸአብያ መሪዎች ይህንን በጋራ የፈጠሩትን ኮሚሽን በአንድ ድምጽ የሚማጸኑት ኢትዮጵያ በግድ እጇ እየተጠመዘዘ ከጣልያን ኮሎንያሊስቶች ጋር ከተፈራረመቻቸው በርካታ ውሎች መሃከል በሶስቱና ከሁሉም ውሎች በላይ ለኢትዮጵያ በጎጅነታቸው በተመረጡ በሚመስሉት የ1900 የ1902 እን የ1908 ውሎች ላይ ተመርኩዞ ውሳኔ እንዲሰጥ ነው። ትንሽ ልዩነት ቢኖር የኢህአዴግ መሪዎች በነዚህ «ምርጥና» ቁንጽል ውሎች አንቀጾች ላይ ብቻ የተመረኮዘ ውሳኔ እንዲሰጥ ሲጠይቁ የሸአብያ መሪዎች ደግሞ የጣልያን ኮሎንያሊስቶች ከነዚህ ውሎች አልፈው ተርፈው በነደፏቸው ካርታዎች ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ይሰጠን ማለታቸው ብቻ ነው።

ፍርድም ሆነ ሽምግልና ሸንጎ ቀርበን ለኢትዮጵያ ጥቅምና ክብር «እንሟገታለን» ቢባል ኖሮ በአድዋ ድል ማግስት በ1897 የተፈረመው የአዲስ አበባ ስምምነትና በተለይ ደግሞ በዚህ ስምምነት መሰረት ጣልያን ባስገዳጅ ውሎች ከኢትዮጵያ እየቀረሰች የምትወስደውን ማንኛውንም ግዛት ወደፊት በአንድ በሆነ ምክንያት ብትለቅ መልሳ ለኢትዮጵያ እንድታስረክብ የተስማማችበት ውል ሆን ተብሎ ወደ ጎን አይተውም ነበር። ለኢትዮጵያ ክብርና ጥቅም ለመሟገት አስፈላጊ የሆነው ራእይ ቢኖር ኖሮ እነዚህ ውሎች በማይመጣጠኑ ሃይሎች መሃከል የተደረጉ የግዴታ ውሎች መሆናቸው ተጠቅሶ ሁኔታዎች ሲቀየሩ አስገዳጅነታቸው ገደል እንደሚገባ የሚደነግገው የአለም አቀፍ የውሎች ህግ በተወሳ ነበር። የብሄራዊ ሃላፊነት ስሜት ቢኖር ኖሮ ከነዚህ ውሎች በኋላ ፋሽሽት ጣልያን መላ ኢትዮጵያን በወረረች ጊዜ በሃይል ይህንን ድንበር ማፍረሷና በዚያውም እነዚህን የድንበር ውሎች በአንድዮሽ እርምጃ መሰረዟ በዚህም ምክንያት በአለም አቀፍ የውሎች ህግ መሰረት በዚህ መልክ በአንዱ ተዋዋይ ወገን የአንድዮሽ እርምጃ የፈረሰ ውል በሌላው ወገን ላይ አስገዳጅነት አይኖረውም የሚለው መሰረታዊ መርህ በተነሳ ነበር። ከዚያም ከጣልያን ሽንፈት በኋላ በ1947 እ.ም. በተደረገው የሰላም ስምምነት መሰረት ቀደም ሲል በሁለቱ አገሮች መሃከል የተደረጉት የጣልያን «የግዛት ይገባኛል» ጥያቄዎች በሙሉ መሰረዛቸው ከቁጥር መግባት ነበረበት።

በሌላውና ብዙ ኢትዮጵያውያንን አስጨንቆ በያዘው በአፋር ህዝብ የኢትዮጵያዊነት መብትና በአሰብ ወደብ ጉዳይም «ሁለት» የተባሉት ወገኖች ለኮሚሽኑ የሚያቀርቡት የተለያየ አቋምም ሆነ ጥያቄ የላቸውም። የአፋር ህዝብ ቅኝ ገዥዎች በኢትዮጵያ ላይ በ1908 እ.ም. የግዴታ ውል መሰረት የጫኑትን ድንበር አሻፈረኝ በማለት ከዚያ ወቅት ጀምሮ ለኢትዮጵያዊነቱና ለራሱም ብሄራዊ አንድነት ሲታገልና ሲሰዋ ቆይቷል። የንሸአብያ የመገንጠል ትግል ሲጠነሰስ ጀምሮ ይህንን ሂደት አልደገፈም። በወያኔ ተባባሪነት በሸአብያ ሙሉ ቁጥጥር ስር ሬፈራንደም ተካሄደ በተባለበት ወቅት ለሱም የራሱን እድል የመወሰን መብቱ እንዲታወቅለትና እሱም ዴሞክራሲያዊ መብቱን ተጠቅሞ የብሄራዊ አንድነት ህልሙን ህያው እንዲያደርግ በደርግ ዘመን በዚህ አንጻር አግኝቶ የነበረው የተወሰነ ድል በጥቂት ጸረዴሞክራሲና ጸረ ኢትዮጵያ ሃይሎች ሴራ ተቀልብሶ እንደገና ተቆራርሶ «የአፍሪካ ቀንድ ኩርድ» እንዳይሆን በተደጋጋሚ ጩኸቱን አሰምቷል። ለዚህ ጥሪው ፍትሃዊ መልስ በማይሰጥ ሁኔታ ተደረገ ለተባለው ሬፈራንደም ተገዥ እንደማይሆንም ለሚመለከተው ሁሉ በወቅቱ ይፋ አቋሙን ገልጿል። በዚህም ሳያቆም ለነጻነቱና ለኢትዮጵያዊነቱ መሳሪያ አንስቶ ሲዋደቅ በሸአብያና በወያኔ ጦር የተባበረ ክንድ በደረሰበት ጥቃት ብዙ መስዋእትንት ሲከፍል ቆይቷል። በዚህም መሰረታዊ ጥያቄ ላይ የወያኔና የሸአብያ መሪዎች በዚህ የሽምግልና ሸንጎ ወገን አስለይቶ የሚያሟግት ምንም ልዩነት የላቸውም።እዚህም ላይ በወያኔ መሪዎች በኩል በሽምግልናም ሆነ በፍርድ ሸንጎ ተከራክረን የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅምም ሆነ «ኢትዮጵያዊ ነኝ» የሚልን አንድ ህዝብ መብት እናስከብራለን የሚል ራእይ ቢኖር ኖሮ ቢያንስ ሁለት መሰረታዊ ክርክሮች ይነሱ ነበር።

አንደኛ ድሮውንም ቢሆን «ከቀይ ባህር ፓራለል ስልሳ ኪሎሜትር እየገባ» የሚለው የ1908 ውል ሆን ተብሎ ኢትዮጵያን ዝግ አገር አድርጎ ለማዳከም የተበጀ ግፈኛ ውል መሆኑና ኢትዮጵያ የባህር በር የማግኘቷ ጉዳይ ፍትሃዊነት ታምኖበት በ1950 እ.ም. በተባበሩት መንግስታት የኤርትራ የወደፊት እድል ከመወሰኑ በፊት ሁለት አመት ቀደም ብሎ በ1948 እ.ም. በወቅቱ የነበሩት አራቱ ሃያላን መንግስታት (ማለትም ዩናይትድ ስቴትስ፤ ታላቋ ብሪታንያ፤ ሶቭየት

ህብረትና ፈረንሳይ) የአፋር ግዛት በሙሉ ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለስ ያደረጉት ስምምነት መቅ ረብ ነበረበት። ይህ አልቀረበም።

ሁለተኛ የአፋር ህዝብ ለብሄራዊ አንድነቱ ባደረገው ያላሰለሰ ታግል በደርግ ዘመን አን ድ የድል ምእራፍ በመድረሱ ኤርትራ በተገነጠለችበት ወቅት ይህ ግዛት የኤርትራ ሳይሆን በራ ስ ገዝ አስተዳደርነት የኢትዮጵያ አካል እንደነበረ ይታወቃል። ይህም በመሆኑ የአፍሪካ አንድ ነት ድርጅት መሪዎች በካይሮ የ1964 እ.ም. ስብሰባቸው የአፍሪካ አገሮች ድንበር እነዚህ አገሮ ች ነጻ በወጡበት ወቅት የነበራቸው ድንበር ይሆናል በማለት ያጸደቁት ስምምነት አሁንም የኢ ትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅምና የአፋርን ህዝብ መብት በሚያስከብር መልኩ መነሳት ነበረበት። ይ ህ አልሆነም።

የወያኔና የሸአብያ መሪዎች በነዚህ መሰረታዊ በሆኑ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅምና የህዝ ቦቿን መብት በሚነኩ፤ ዞሮ ዞሮ ደግሞ ለወደፊቱ የአካባቢው ሰላም ቁልፍ ናቸው ብለን በምና ምናቸው ጥያቄዎች ላይ መሰረታዊ የሚባል ልዩነት የላቸውም። በመሆኑም የሽምግልናው ኮሚ ሽን «የሁለት ወገን ክርክሮች» ብሎ የሚያዳምጠውና የሚፈርድበት ነገር አይኖርም።

ኢትዮጵያ መብትና ክብሯን ለማስከበር ራእዩና ቁርጠኝነቱ ያለው መንግስት ባልታደለች በት በአሁኑ ወቅት እነዚህን ሁሉ ጥያቄዎች እያነሱ ብዙ አገር ወዳድ ምሁራን፤ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ድርጅቶችና ሌሎች ስብስቦች ለተባበሩት መንግስታት ድርጅት፤ ለአፍሪካ አንድነት ድርጅት፤ ለድንበር ሽምግልናው ኮሚሽን፤ ለምእራብ መንግስታትና ለሌሎች ለሚመለከታቸው ሁሉ ባላሰለሰ ሁኔታ ደብዳቤዎችና ማመልከቻዎች እያጎረፉ ይገኛሉ።

ኢተፖድህ በዚህ የሽምግልና ኮሚሽን ጉዳይ ከነዚህ አገር ወዳድ ሃይሎችና ከመላው የ ኢትዮጵያ ህዝብ የተለየ አቋምም ሆነ ራእይ የለውም። በወያኔና ሸአብያ መሪዎች ተመርጦ፤ በ ነዚሁ ሃይሎች በቀረበለት አጀንዳ ብቻ ተወያይቶ፤ ሌሎች ክርክሮችንም ሆነ መረጃዎችን እን ዳይመረምር ታግዶ ብያኔ ሰጥ ከሚባል ኮሚሽን የኢትዮጵያ ህዝብ ምንም መጠበቅ አይችልም ። በእዳን ሃይሎችም ቢሆኑ ከእናት ትሻል ሞግዚት ሆነው ኢትዮጵያዊ ነኝ ብሎ ከሚገዛ መን ግስት ይበልጥ ለኢትዮጵያ ቆመው ሊከራከሩ አይችሉም። ይህ የኛ የኢትዮጵያውያን አደራና ተግባር ነው። በዚህ አንጻር ትግላችንን አቀነባብረን ኢትዮጵያውያን የኛ የሚሉት ኢትዮጵያን የ ኔ የሚል ዴሞክራሲያዊና ብሄራዊ መንግስት ለማቋቋም ዛሬ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ መነሳሳት ይኖርብናል። በዚህ መልክ ከፊታችን ለተደቀነው አዲስ የትግል ምእራፍ ስንነሳሳ ትኩረት ያስ ፈልጋቸዋል ከምንላቸው ብሄራዊ ተግባራት መሃከል ሶስቱን ብንጠቅስ

<u>አንደኛ</u>፣ ሁሉም ይንቀሳቀስ። ከዚህ ኮሚሽን ይፈልቃል የሚባለው ውሳኔ የኢትዮጵያን ታሪካዊና ህጋዊ መብቶች ሳይመረምር፣ በኢትዮጵያ ስም ማንኛውንም አስገዳጅ ውል ለመፈራረ ምም ሆነ ውሳኔ ለመቀበል ከህዝባችን የተሰጠ ምንም ውክልና፣ በዴሞክራሲያዊ ሂደት ያገኙት ምንም የፖለቲካ ተአማኒነትና ህጋዊነት፣ በህዝብ ከበሬታ የተጎናጸፉት ምንም አይነት የሞራል ብቃት በሌላቸው ከራሳቸው በስተቀር በማንም ስም ለመናገር በማይችሉ ሃይሎች የሚደረግ ው ል ኢትዮጵያን ሊያስሪት አይችልም ከሚለው አቋም አንጻር የወያኔ መሪዎች አጉል አጸፋ ምን እንደሚሆን ከወዲሁ ግልጽ ነው። ይህንን የሃገር ፍቅር ትግል የጥቂት «ከራሳቸው በስተቀር ማ ንንም የማይወክሉ» ጸረ ሰላምና ጸረ ዴሞክራሲ ሃይሎች መፍጨርጨር አስመስለው ለማቅረብ ይሞክራሉ። በመሆኑም ይህ አገር ወዳድ ምሁራን፣ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ድርጅቶችና ሌሎ ች ስብስቦች የተሰማሩበት የተቃውሞ እንቅስቃሴ የመላው ህዝብ እንቅስቃሴ መሆኑን ለማሳየት ፣ ይህንን ውሳኔ ከወዲሁ መቃወም የሚያስፈልገው «ከጦር ጠማሽነት» አቋም በመነሳት ሳይሆ ን እንዲያውም በዚህ ኢፍትሃወዊ ውሳኔ ሳቢያ ለአካባቢያችን ሰላም ከፍተኛ አደጋ እንዳይከተ ል በማሰብ መሆኑን ለማስረገጥ፤ አለም አቀፉ ኮሙኒቲ ይህንን ውሳኔ በጭፍን ከደገፈ ለሚከተ ለው ጥፋት እስተዋጽኦ የማድረግ አደጋ እንዳለ ለማስጠንቀቅ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገ ር ሁሉም በሰፊው የሚሳተፍበት እንቅሳቃሴ ማካሄድ እጅግ አስፈላጊ ነው።

ሁለተኛ ትግሉ የኮሚሽኑን ውሳኔ ከመቃወም አልፎ የሚሄድ ሰፊና ዘላቂ እንቅስቃሴ እን ዲሆን ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። ዛሬ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ የችግራችን ሁሉ ምንጭ ኢ ትዮጵያችን ምንም አይነት ሃገራዊ ራእይ በሌላቸውና ያለ አንዳች ተጠያቂነት አገራችንን በአፈ ና በሚገዙ ጥቂቶች ቁጥጥር ስር የወደቀች መሆኗ ለማንም ግልጽ ስለሆነ በኢፍትሃዊውና ጸረ ኢትዮጵያው ውሳኔ ተቀስቅሶ የሚነሳው እንቅስቃሴ ተቃውሞን ከማስመዝገብ አልፎ የሚሄድ «የኛ» የምንለው ብሄራዊና ዴሞክራሲያዊ መንግስት ለመመስረት የሚደረገው ትግል የማይነጠል አካል ሆኖ መቀጠልና መፋፋም ይገባዋል።

ሶስተኛ ተቃዋሚ ሃይሎች ይህንን ትግል ለማስተባበርና አቅጣጫ ለመስጠት በጋራ መንቀ ሳቀስ ይጠበቅባቸዋል። በዚህ ኢፍትሃዊ ውሳኔ ገንፍሎ ሊወጣ የሚችለው የህዝብ ቁጣ ዛሬ ስራ ተኛው፤ ነጋዴው፤ ገበሬው፤ ወጣቱ፤ ስራ አጡ በአጠቃላይ የህብረተሰቡ የተለያዩ ክፍሎች ከ ሚያነሷቸው የመብትና የህልውና ጥያቄዎችና ትግሎች ጋር ተደማምሮ በአለፈው አመት ከታዘ ብነው ይበልጥ የሰፋ የህዝባዊ ብሶት ማእበል ሊከሰት የሚችልበት ሁኔታ የማንጠብቅበት ምክን ያት የለም። እስካሁን እንደታየው ሁሉም ከሞላ ጎደል በግብታዊነት ተራ በተራ እየተነሳ ተራ በተራ ለወያኔ ጥቃት የሚጋለጥበት ሁኔታ እንዳይኖርና ሊከሰት ከሚችለው ከባድ የፖለቲካ ቀ ውስ በድል አድራጊነት ለመውጣት ከተፈለገ በትግል ላይ ያሉት የህብረተሰብ ክፍሎች በሙሉ ተቃዋሚ ሃይሎች የሚያቀርቡትን የጋራ አማራጭ ከትግል አጀንዳቸው እንዲያካትቱት የሚደረ ገው ጥረት ዛሬ ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ አጣዳፊና አንገብጋቢ መሆኑን በመረዳት ዴሞክራሲያ ዊ ድርጅቶች በግልጽና ዴሞክራሲያዊ አማራጫቸው ዙሪያ ህብረታቸውን አጠናክረው ለመንቀሳ ቀስ እጥፍ ድርብ ትግል ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

የኢተፖድህ ሴክሬታርየት
ፍራንክፈርት ( ጀርመን )
ጥር 21 ቀን 1994 ዓ.ም.

•